ሕገ መንግሥታዊ የዘውድ አስተዳደር ምንድን ነው ?

ሕገመንግሥታዊ የዘውድ አስተዳደር ወይም በእንግሊዝኛው አጠራር "የኮንስቲቱሽናል ሞናርኪ አስተዳደር" ምን ይመስላል ?

ለአንድ አገር የሚያስገኘው ጥቅምስ አለ? ለሀገራችንስ ኢኮኖሚያዊ ፤ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጠቀሜታው እስከምን ድረስ ነው ?

ኢትዮጵያ አገራችን ጥንታዊት ገናናና የታላቅ ስልጣኔ ባለቤት የነበረች ፤ ለብዙ ሺህ ዓመታት ሉዐላዊነቷና ነፃነቷ በዘውድ ድባብ ስር በሕዝቦቿ አንድነትና ተጋድሎ ተጠብቃ የኖረች አገር ናት ።

የአገሪቱ ብሔረሰቦችና ልዩልዩ ማህበረሰቦችም በባህል መወራረስ ፤ በጋብቻ ፤ በማህበር ፤ በወንፈል ሥራ ፣ በሀዘንና በደስታ ዘመን ፤ በሰላምና በጦርነት ጊዜ በዘውድ ድባብ (ጥላ) ስር ተሳስረው በአንድነታቸው ጸንተው የኖሩ ሕዝቦች ለመሆናቸው ምስክራቸው ታሪክ ነው ።

የኢትዮጵያ የረጅም ዘመን የነፃነት ታሪክ የብሔረሰቦችዋ የጋራ ህልውናና የጋራ ታሪክ ነው ።

ምንም እንኳን ባለፉት ፲፯ አመታት ሕዝብን ለማወናበድና ታሪክን ለማዛባት አያሌ ሙከራዎች ቢደረጉም ዘውድ የኢትዮጵያን ብሔረሰብ ሁሉ እንደ አንድ ቤተሰብ አስተሳስሮ የኖረ የሰላም የፍቅር የስምምነትና የአንድነት ምልክት በመሆኑ ሁሉን በማቀፍ አማራ ፤ ኦረሞ ፤ ትግሬ ፤ ጉራጌና ወዘተ ሳይል አሰባሳቢ አካል በመሆን በኢትጵያ ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ሚና ሲጫወት የቆየ ኃይል ነው ።

በመሆኑም ዘውድ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ቅርሱ ኩራቱና የአንድነት ምልክቱ ነው ።

ስለዚህም ምልክትነቱና ጌጥነቱ ምንጊዜም ይፈለጋል ።

አገራችን አሁን ባለችበት ሁኔታ የተለያዩ ዓለም መንግሥታትና ካፒታሊስቶች በተለያዩ ኢኮኖሚያዊ ዘርፎች ተሳትፎ (ኢንቨስት) እንዲያደርጉ ትልቁ ዋስትናቸው ሊሆን የሚችለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪካዊ ቅርሱን አክብሮ በዘውድ ድባብ ስር ተሰባስቦ በአንድነቱ ጸንቶ ጦርነትንና መለያየትን አስወግዶ በሰላም መኖር ሲችል ብቻ ነው ። አለበዚያ ቅቤ እሳት ላይ እንደማይጥሉ ለማንም ግልጽ ነው ። ለዚህም ነው በርካታ የዓለም መንግሥታት በተለይም ምዕራባውያን የንጉሠነገሥት ግርማዊ ቀዳዊ አጼ አምኃ ስላሴን ወደአገራቸው መመለስና ኢትዮጵያም ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍላት የቆየውን ታሪኳን ጠብቃ እንደ እንግሊዝና ጃፓን በሕገመንግሥታዊ ዘውድ አስተተዳደር እንድትመራ የሚፈልጉት ።

ለመሆኑ በሕግ በተወሰነ የደንብ ክልል ውስጥ የስልጣን ገደብ ተደርጎለት የሚሰራ ህገመንግሥታዊ አስተዳደር ምን ይመስላል ?

በእንግሊዝ አገርና በጃፓን እንደሚታወቀው ሥልጣኑ በህግ የተወሰነለት ታሪካዊ ቅርስ የሆነ የዘውድ አስተዳደር በውስጡ ብዙ ፓርቲዎች የሚኖሩበት የሕዝብ ዲሞክራሲ መብት ተከብሮ በሕዝብ ምርጫ ሀገሪቱን የሚያስተዳድሩ ልዩልዩ የፖለቲካ ፓርቲዎችና የኢኮኖሚ መዋቅሮች የሚገኙበት ሥርዓት ነው ።

ይህንንም በኢትዮጵያ እውን ለማድረግ ያገሪቱ የበላይ ህግ የሚሆነውና የምትተዳደርበት ሕገመንግሥት በሚቀረጽበት ወቅት የሚከተሉትን ነጥቦች የሚያካትት ይሆናል ።

፩ ዘውድ የኢትዮጵያ ታሪካዊ መታወቂያ በመሆኑ የሺ ዘመናት ስርወ መንግሥቱን ተከትሎ ከትውልድ ወደ ትልድ በመተላለፍ የህዝቧን ልዕልናና የአገሪቱ ሉአላዊነት የሚረጋገጥበትና የዘውድ አገር መሆኗም በግልጽ ይቀረጻል ።

፪ ዘውድ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ አሰባሳቢ አካል በመሆን ያገሪቱን አንድነትና ሰላም በማስጠበቅ ከፍተኛና ወደር የሌለው አስተዋጽዖ ሲያበረክት የኖረ ኃይል መሆኑና አስፈላጊነቱ ይረጋገጣል ።

፫ ዘውድ ከታሪካዊ ቅርስነቱ ባሻገር ለሰላምና ለኤኮኖሚ ግንባታ ለውጭ ኢንቨስተሮችና ኢንተርፕሩነሮች አስተማማኝ ዋስትና መሆኑም ይረጋገጣል ።

፬ ዘውድ በሕዝቦች አንድነትና በሕግ ልዕልና ላይ የተመሠረተ ይሆናል ።

፭ የፍርድ ቤቶች ፣ የመንግሥት ምክር ቤትና ሌሎችም ተቋማት ከዘውድ ተፅዕኖና ግፊት ነፃ መሆናቸውም ይረጋገጣል ።

፮ በአጠቃላይም በተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ እ-ኤ-አ- በዲሰምበር ፲ ቀን ፲፱፻፵፰ ዓ- ም- የጸደቀውንና የታወጀውን ቁጥር ፪፻፲፯ ውሳኔ መሠረት በማድረግ የግለሰብ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ያለአንዳች ገደብ ሙሉ በሙሉ የሚከበሩበት መሆኑ ይረረጋገጣል ።

፯ እነዚህንም መሠረታዊ ሃሳቦችን የሚያጠናክሩ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነትና ሰላም አዎንታዊ ተፅዕኖ የሚያደርጉ ህጎችንና ደንቦችን ሁሉ በሚያጠቃልል ሕገመንግሥት የሚመራ ይሆናል ።

ከዚህም ባሻገር ለአንድ ወጥ ሕብረ ብሄር ሥርዓት መመስረትና በፖለቲካ በኢኮኖሚና በማህበራዊ ኑሮ ግንባታ ቅንጅታዊ ክስተቶችን ለማመቻቸትና በብሔረሰቦችና በሀይማኖት ልዩነት የሚነሱትን ግጭቶች ለማስወገድና በአንድነት በአንድ አላማና ግብ ለአንዲት ታላቅ ኢትዮጵያ ግንባታ ሕገመንግሥታዊ የዘውድ አስተዳደር አማራጭ የለሽ ፍቱን መፍትሂ መሆኑ ጤናማ አመለካከት ላለን ዜጎች ሁሉ ከግንባር የፈጠጠ ገሃዳዊ እውነታ ነው ።

ለዚህም ጃፓንና እንግሊዝ እንዴት ሰለጠኑ? በምጣኔ ሀብት (በኢኮኖሚ) ልማትስ እንዴት ሊስፈነጠሩ እንደቻሉና የታሪክ ቅርሳቸው የሆነው የዘውድ አስተዳደርስ ለዚህ ስልጣኔና ልማት ያበረከተው አስተዋፅኦ እስከምን ድረስ ነው የሚለውን ለማወቅ በየምዕራፉ የታሪክ ማህደርን ከማገላበጥና ዛሬ ጃፓንም ሆነች

እንግሊዝ የደረሱበትን የቴክኖጂና የልማት ደረጃ በአንክሮ ከማስተዋል ባሻገር ሌላ ምን መረጃ ያሻል? ግልፅ ለሆነ ነገርስ ምን ማብራሪያ ያስፈልገዋል?

አገራችን በአሁኑ ጊዜ ከምትገኝበት አስጊና አስፈሪ አዝማሚያ እንዲሁም ኋላቀር ከሆነው የቴክኖሎጂ የዕድገት ደረጃ ተላቃ በሰላማዊ መንገድ የልማት እመርታ ወደምታሳይበት ደረጃ ለማሸጋገር ሂደቱ ከዘውድ ህልውና እውን መሆን ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው ።

እንኳን ኢትዮጵያን ያህል ታላቅ የታሪክ መዘክርና ጥንታዊ ገናናስልጣኔ ባላት አገር ቀርቶ በእንግሊዝና በጃፓን እንኳን ነገሥታቱን ብቻ ለማየት ወደየሐገሮቹ የሚተመው የአገር ጎብኝዎች ቁጥር ለየአገሮቹ ተወላጆች ታላቅ ኩራትና ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ማግኛ ዘዴ ፈጥሮላቸዋል ። እንዲህም ሲል ጎብኝዎችን ለማስተናገድ በሚደረገው የሆቴል የአየር መንገድ የሌሎችም ድርጅቶች የሥራ እንቅስቅስቃሴ መጎምራት የሥራ ዕድል ለመፍጠርና ባህልንም ለማዳበር የሚኖረውን አስተዋጽኦ ከኢኮኖሚው ጠቀሜታ ጋር አዳምረው በጥቅሉ በማየት ቅርሳቸውን በሚገባ ይንከባከቡታል ።

ከዚያም ባሻገር የኢትዮጵያ ሕዝብ የአንድነትና የታሪክ አርማው ተከብሮ በእኩልነት ላይ በተመሠረተ ወንድማማች መንፈስ በአንድ ወጥ አብሮ የኖረውን ያህል ወደፊትም የሚኖርበትን ሥርዓትና መዋቅር ዘርግቶ እንዲት ታላቅ ኢትዮጵያን ቀድሞ በነበራት ታላቅ ክብር ታሪክና ነጻነት ለማቆየት የሕግ መንግሥታዊ ዘውድ አስተዳደር አስፈላጊነት አጠያያቂም የሚካድም አይደለም ።

ታሪክ ውሉን እንዳይስት በስደት አገር ሳይቀር ቅርሳችንን ለማቆየት የታገሉልንን ንጉሠ ነገሥት አፄ አምሐ ሥላሴ ፤ ንጉሣውያን ቤተሰቦች ፤ የሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካልና ሌሎችም ደጋፊዎቻቸው ለሀገራቸው ባላቸው ቀናኢነት በእጅጉ ሊመሰገኑ ይገባል ።

በእሾህ መሐል እንደበቀለች ጽጌረዳ መከራ የጠናባትን አገራችንን ሀያሉ እግዚአብሔር በቃሽ ብሎ ንጉሠ ነገሥትዋን በሰላም ለምድራቸው ያብቃላት ።